# ማርያም ደስ ይበልሽ

ማርያም (3X) ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ } **አዝማች...**
በአንቺ ስለ አደረ የዓለም ሁሉ ጌታ

የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሃን

**አዝማች...**

መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ

**አዝማች...**

ገብርኤል (2X) ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋን በመልበስ

**አዝማች...**

በቤተ መቅደስም ተቀምጣ ድንግል
ሐርና ወርቁን አስማምታ ስትፈትል

**አዝማች...**

ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ

**አዝማች...**

እውነተኛው ንጉሥ መሆኑን ስለ አየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

**አዝማች...**

# ማርያም እመቤቴ

ማርያም እመቤቴ የአምላክ እናት
ማደሪያ የሆንሽው ዙፋን ለመለኮት
ከሴቶች ሁሉ አንቺ ነሽ
የተባረክሽ የንፃሽ በእውነት

} **አዝማች...**

ከቶ እንደምን ቻልሽው መድኃኔዓለምን
ሰማይና ምድር የማይችሉትን
ለዚህ የተመረጥሽ ታላቅ እድለኛ
ምሕረትን ከልጅሽ ለምኝልን ለኛ

**አዝማች...**

የነቢያት ሞገስ የሐዋርያት
የሰማዕታት አክሊል የጻድቃን እናት
የእኛ መመኪያችን የኃጥአን ተስፋ
ወልድን በመውለድሽ ኃዘናችን ጠፋ

**አዝማች...**

ቅዱሳን በገነት ሲያመሰግኑሽ
መላእክት በሰማይ ሲያገለግሉሽ
እኛም የአዳም ልጆች በምድር ሆነን
በኣሊ ለነ ቅድስት እንልሻለን

**አዝማች...**

ምንኛ ድንቅ ነው ምሕረቱ የወልድ
የእንቺን ሥጋ ለብሶ ሲሆነን ዘመድ
ከዙፋኑ ወረዶ ያገለገለሽ
የሕይወት ሙሽራ ማርያም አንቺ ነሽ

**አዝማች...**

# እርሱ ባይወለድ

እሰይ እሰይ ተወለደ (2X)
ከሰማያት ሰማይ ወረደ (2X) } **አዝማች...**
ከድንግል ማርያም ተወለደ

እርሱ ባይወለድ (እሰይ እሰይ) ቸሩ አባታችን (እሰይ እሰይ)
እርሱ ባይወለድ » » መድኃኒታችን » »
መች ትገኝ ነበረ » » ገነት ምድራችን » »

**አዝማች...**

እንደጠል ወረደ (እሰይ እሰይ) ከሰማይ ወደ እኛ (እሰይ እሰይ)
ወገኖቹን ሊያድን » » ከክፉ ቁራኛ » »

**አዝማች...**

ብርሃን ወጣላቸው (እሰይ እሰይ) ለእምነት ወገኖቹ (እሰይ እሰይ)
የጨለማን ጉዞ » » እንዲያ ሲሰለቹ » »

**አዝማች...**

እግዚአብሔር አብ ላከ (እሰይ እሰይ) አንድያ ልጁን (እሰይ እሰይ)
እርሱ ወዷልና » » እንዲሁ ዓለሙን » »

**አዝማች...**

# የምሥራች እልል በሉ

የአምላካችን ክብሩ ይስፋ
ምስጋናውም ይንሰራፋ
ሰዖልናል ታላቅ ተስፋ
ወገኖቹ እንዳንጠፋ

የምሥራች እልል በሉ
ችግረኞች ድሆች ሁሉ
የምሥራች እልል በሉ
} **አዝማች...**

ተሰናዱ በውል ሁኑ
እንድንዘምር ለሕፃኑ
ወርዶ መጥቷልና ከዙፋኑ
ቤዛ ሊሆን ለወገኑ

**አዝማች...**

አምላካችን ደጉ አባት
ባለብዙ ቸርነት
ወገኖቹ እንዳንሞት
ሰደደልን መድኃኒት

**አዝማች...**

የዳዊት ልጅ ሆሳዕና
ይገባዋል ክብር ምስጋና
ለእርሱ ችግር ለእኛ ጤና
ከዙፋኑ ወርዷልና

**አዝማች...**

ባጎደሉት ሰዎቻችን
አስሮን ነበር ጠላታችን
ከፋይ ሰዶ ለዕዳችን
ባሮች ሆንን ለአምላካችን

**አዝማች...**

በጎል በጎል
በጎል በጎል ሰብአ ሰገል በጎል ሰብአ ሰገል (2)
በጎል ሰብአ ሰገል ሰገዱለት (2)

ድንግል ማርያም ንጽሕት ቅድስት (2)

የጌታዬ እናት ምስጋና ይገባሻል
ከሴቶች ሁሉ ባንቺ አድሮብሻል (2)

ፀሐይ ፀሐይ ፀሐይ ሠረቀ (2)
ፀሐይ ሠረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ (2)

በጎል በጎል አማኑኤል በጎል አማኑኤል (2)

እግዚአብሔር ፍቅሩን ሲገልጽልን
አንድያ ልጁን ለኛ ሰጠን (2)

እልል እልል ደስ ይበለን እልል ደስ ይበለን (2)

መድኅን ተወልዶ ነጻ አወጣ
ዮሐንስ አጥምቆ ድል አገኘን (2)

አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ (2)
የእግዚአብሔር ከላይ ወርዶብሽ
የዓለም መድኃኒት ተጠመቀብሽ (2)

ከድንግል ተወልዶ

ከድንግል ተወልዶ እኛን ሊቀድስ
ተጠመቀ ኢየሱስ በባሕረ ዮርዳኖስ
መጥምቁ ዮሐንስ ምንኛ ታደለ
ዮርዳኖስስ ወርዶ ለምን ኮበለለ
ትንቢቱን ሊፈጽም አስቦ ክርስቶስ
ተጠምቆ አዳነን በባሕረ ዮርዳኖስ

ከድንግል............
ምስጢረ ስላሴ ታየ የዚያን ለታ
በምን ይከፈላል የጥምቀት ውለታ

ከድንግል............
እሳተ መለኮት አምላክን ወለድሽ
እኛኑ ለማዳን አፍቅሮ ልጅሽ

ከድንግል..........
እመቤቴ ማርያም ምንኛ ታደልሽ
ካዳም ልጆች ሁሉ አንቺ ተመርጥሽ

ከድንግል........
ቸሩ አምላካችን መድኃኔዓለም
ኑ እናመስግነው ባንድ ላይ ሆነን
ከድንግል ተወልዶ እኛን ሊቀድስ
ተጠመቀ ኢየሱስ በባሕረ ዮርዳኖስ
መጥምቁ ዮሐንስ ምንኛ ታደለ
ዮርዳኖስስ ወርዶ ለምን ኮበለለ

# አሰይ ተወለደ

እንዴት የበዛ ነው የአምላክ ቸርነቱ
ኀልቶ ሳይታየው ፍጹም መሳሳቱ
የሰው ፍቅር ስቦት ከታላቅ ዙፋኑ
ወደ ዓለም መምጣቱ በአካል መወሰኑ
ደስታችን ይብዛ እንዘምር በእልልታ
ክብርን ላወረሰን ለምሕረቱ ጌታ
በዓለም ተሰበከ የምሕረት አዋጅ
ተወልዶ ሲጠመቅ በዮሐንስ እጅ
ተወለደ አሰይ ተጠመቀ አሰይ ለማዳን እኛን
ተወለደ አሰይ ተጠመቀ አሰይ ለማዳን እኛን
በደላችንን ሽሮ ወልዶን በልደቱ
እነጻን ከእድፍ በማየ ጥምቀቱ
ዮርዳኖስም ሲሸሽ ባሕርም ስትፈራ
በውሃ ታጠበ የሰው ልጅ መከራ
ደስታችን ይብዛ እንዘምር በእልልታ
ክብርን ላወረሰን ለምሕረቱ ጌታ
በዓለም ተሰበከ የምሕረት አዋጅ
ተወልዶ ሲጠመቅ በዮሐንስ እጅ
ተወለደ አሰይ ተጠመቀ አሰይ ለማዳን እኛን
ተወለደ አሰይ ተጠመቀ አሰይ ለማዳን እኛን

# እምላካችን መድኃኒታችን

አዳምን ያልተወው እንደተሰደደ
እሰይ የምሥራች ዛሬ ተወለደ

እምላካችን መድኃኒታችን
ተወለደ ለነፃነታችን } **አዝማች...**

አዳምን ያልተወው እንደተጨነቀ
እሰይ የምሥራች ዛሬ ተጠመቀ

**አዝማች...**

አዳምን ለመጥራት የመጣው ሙሽራ
በገሊላ መንደር ለሠርግ ተጠራ

**አዝማች...**

ሠርግ ቤት እንዳለ በክብር ተቀምጦ
የወይን ጠጅ ሆነ ውኃው ተለውጦ

**አዝማች...**

በገሊላ አውራጃ ይሆን ተአምር ሰራ
እጅግ ያስደንቃል የእምላካችን ሥራ

**አዝማች...**

ጌታችን አንድ ቀን ያደረገው ተአምር
ሲያስደንቅ ይኖራል ይህን ሁሉ ፍጡር

**አዝማች...**

# የዓለምን በደል

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ
ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ

የሰለሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ } **አዝማች…**

የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉሥ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደ ፈረስ

**አዝማች…**

ባሕር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
እንደ ተናረው ዳዊት በትንቢቱ

**አዝማች…**

ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሠርት
መጣ በደመና ሰማያዊው አባት
እየመሰከረ የልጁን ጌትነት

**አዝማች…**

እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ
በርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ

**አዝማች…**

ባሕር ስትጨነቅ ተራራው ሲጨፍር
ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይህን ምስጢር

**አዝማች…**

www.ethiopianorthodox.org

ዮሐንስኒ ያጠምቅ (2X)
በሐሴኖን (4X) በማዕዶት ዮርዳኖስ
ዮሐንስ ሲያስተምር (ያጠምቅ)
በጫካ በሜዳ (ያጠምቅ)
ግመል ጸጉር ለብሶ (ያጠምቅ)
ሆኖ ምድረ በዳ (ያጠምቅ)
በሐሴኖን (4X) በማዕዶት ዮርዳኖስ
አምላኩን የሚወድ (ያጠምቅ)
ብዙ ሰው እያለ (ያጠምቅ)
ጌታውን ለማጥመቅ (ያጠምቅ)
ዮሐንስ ታደለ (ያጠምቅ)
በሐሴኖን (4X) በማዕዶት ዮርዳኖስ
ከኃጢአት ተለዩ (ያጠምቅ)
በውሃ ተጠመቁ (ያጠምቅ)
መንግሥተ ሰማያት (ያጠምቅ)
እንዳለች እወቁ (ያጠምቅ)
በሐሴኖን (4X) በማዕዶት ዮርዳኖስ

# <u>በዛሬው ጥምቀቱ</u>

በዛሬው ጥምቀቱ ተነግሮ አዋጅ
ነፃ ነፃነት በእግዚአብሔር አብ ልጅ
<u>ደስ ይበልሽ</u> (2X) ደስ ይበልሽ ደስ ዮርዳኖስ

አብም መሰከረ በደመና ሳለ
የም የምወደው ልጄ ይሄ ነው እያለ
<u>ደስ ይበልሽ</u> (2X) ደስ ይበልሽ ደስ ዮርዳኖስ

ጌታ በዮሐንስ ሊጠመቅ ሲል ገና
ወደኋላው ሸሸ ዮርዳኖስ ፈራና
<u>ደስ ይበልሽ</u> (2X) ደስ ይበልሽ ደስ ዮርዳኖስ

እንደ አምቦሳ ጥጃ ተራሮች ዘለሉ
አፁብ አፁብ ነው ድንቅ ነው ምን ይገርም እያሉ
<u>ደስ ይበልሽ</u> (2X) ደስ ይበልሽ ደስ ዮርዳኖስ

ውሃውን ወይን አረገ ከተጠራበት ቤት
የብር የብርሃናት ጌታ የዓለም መድሃኒት
<u>ደስ ይበልሽ</u> (2X) ደስ ይበልሽ ደስ ዮርዳኖስ

# ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስ ነያ

ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስ ነያ (2X) } **አዝማች...**
ሃሌሉያ (4X)

ጌታችን ሲጠመቅ ባሕር ምን አለች
አልችለውም ብላ ወደ ፊት ሸሸች
ብርሃን መለኮት በወንዙ ሲሞላ
ዮርዳኖስም ሸሸ ቀረ ወደ ኋላ

**አዝማች...**

ማን ነበር የመጣው ደመናውን ጭኖ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በእርግብ አምሳል ሆኖ
ለልጁ ምስክር ሊሰጥ ፈለገና
አብም ተናገረ ሆኖ በደመና

**አዝማች...**

ጌታችን ሲጠመቅ በሠላሳ ዓመት
ባሕር ኮበለለች ግዑዟ ፍጥረት
ሰማይ ተከፈተ ወኮነ ፀአዳ
ክሩቅ መጥቷልና አብ ታላቁ እንግዳ

**አዝማች...**

እልል በይ ዮርዳኖስ የዕድቅ መገኛ
የሕይወት መሰላል ድህነታችን የእኛ
ቀላያት አብረኸት ብዙዎች እያሉ
እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ

**አዝማች...**

# ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመሔር (2X)
እስመ ለዓለም ምሕረቱ እስመ ለዓለም (2X)

እናመሰግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ (2X)
የዓለም ቤዛ ነውና የማኅጸንሽ ፍሬ (2X)

በድንግልና የወለድሽው የአንቺ ፅንስ (2X)
ለድኩማኖች ብርታት ነው ለሕሙማን ፈውስ (2X)

ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ (2X)
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ (2X)

በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ እዳችንን ፋቀ (2X)
በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን (2X)

እመቤታችን እናታችን ማርያም (2X)
የተማፀነሽ ይኖራል ለዘለዓለም (2X)

ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ (2X)
በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ (2X)

# አማን በአማን

አማን በአማን አማን በአማን (2X)
ኧኸ...መንክር ስብሐተ ጥምቀቱ (2X)
ትርጉም፤ እውነት በእውነት
የክርስቶስ መጠመቅ ግሩም ነው

---

# እንዘ ስውር እምኔነ

እንዘ ስውር እምኔነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ (2X)
ተኣምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ በቃና ዘገሊላ
ከብካበ ኮነ ማየ ረሰየ ወይነ (2X)

ትርጉም፤ ከእኛ ስውር ሲሆን አሁን ግን የታወቀ

ግልጽ ሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃና

አውራጃ የሚያስደንቅ ተአምራትን ተደረገ

ውኃውንም ለውጦ ወይን አደረገው።

---

# በእደ ዮሐንስ

በእደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ (2X)
ሰማያዊ (5X) ኢየሱስ ናዝራዊ (2X)

ትርጉም፤ የናዝሬቱ ኢየሱስ በዮሐንስ

እጅ ተጠመቀ።